# ጃል እኮ ተጠየቅ!

(ከሰሎሞን አሰፋ)

ያልሆነውን ሁኖ፣ ያልሠራውን ሠርቶ፣
ንጹሕ መሥሎ ቀርቦ፣ በክህደት ድሪቶ፣
ያሥደምጡን ጀመር፣ ተጠያቂነትን፣
ሃቁ ተካደና፣ ዜሮ መርሻነትን።

ትግሉን ለማሥቀጠል፣ በሠማዕታት ምለው፣
ኮሚቴውን መርጠው፣ አመራር አውርደው፣
የኢሕአፓ ጀግኖች፣ ጉባኤ ተቀምጠው፤
ጉዳዩ እንዳይጋለጥ፣ ሃቅ ነጥሮ እንዳይወጣ
ማነው ከውይይት፣ የሻተ ፍርጠጣ?!
በላ ልበልሃ! ጃል እኮ ተጠየቅ!
ሃቅን ዋስ እጠራ፣ ማተቤን እሰንቅ!
በውነት ልመሰክር፣ አንዲትም ሳልደብቅ::
ትውልድና ታሪክ፣ ይሁኑኝ ጠበቃ!
ሂሳብም ሳይዘጋ፣ ሰው ከ'ንቅልፍ ሳይነቃ፣
ማነው ፈርጥጦ፣ ሂያጂ ሌሊት በጨረቃ?

ልጠየቅ ካለክማ፣ እኮ ልጠይቅህ?!
ሁሌም አሣፋሪ! ሲመዘዝ ታሪክህ!
ቀድሞም በብተና፣ አሁን ባንጃነትህ፣
ግፉን የጫንክባት፣ ክሕደቱ በዝቶብህ!
ምን በድላህ ይሆን?! ኢትዮጵያ ሃገርህ!?
ውሸትና ቅጥፈት፣ የዶክትሬቱ ዓርማ፣
በክህደት ተለክፎ፣ ሃገርን ሊያደማ፣
ሊያስተምረን ዳዳው፣ በጨረቃ እሩጫ፣
በደንብ ሊያመቻቸን፣ ለወያኔ ጡጫ፣
ለሰላሳ ዘጠኝ፣ አንቀጽ መገለጫ፣
ኢትዮጵያን ሊያስገባ፣ በዘር መስመር ቅርጫ፣
ደብተራው፣ ይስሀቅ፣ አበራሽ፣ ሌሎቹም
ጓዶች ተረሱና፣
ፍጥምጥሙ ሆነ፣ ከነ ሥየ ኣረና፣
ጃል እኮ ተጠየቅ?! የፓልቶኩ ጀግና!?
ያልሆነውን ሁኖ! ያልሠራውን ሠርቶ!

ንጹህ መሥሎ ቀርቦ፣ በክህደት ድሪቶ!
ያሥደምጡን ጀመር፣ ተጠያቂነትን፣
ሃቁ ተካደና ዜሮ መርሻነትን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!